በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፫


መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**መጋቢት ፲፰ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.**

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፫</u>

## <u>የእምነት ዓይነቶች</u>

### 1. <u>*የኀልዮ (ንድፈ-ሐሳባዊ ) እምነት*</u>

- ይህ ዓይነት እምነት በፍልስፍና ወይም በምርምር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት እምነት ያላቸው የእግዚአብሔርንና የማይታዩ ነገሮችን ኀልውና በሕይወት ላይ ተጽእኖ የላቸውም በሚል አእምሮአዊ ፍልስፍናና ላይ ተመርኩዘው ያምናሉ፡፡
- አጋንንትም ይህ ዓይነት እምነት እንዳላቸው የሚያረጋግጡልን ነገሮች አሉ፡፡
- ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ‹‹እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።›› <u>*ያዕ 2፡19፡፡*</u> በማለት ሥራ ስለሌለው እምነት ሲያስረዳ የነገረን ስለዚህ ንድፈ - ሐሳባዊ እምነት ነው፡፡
- ኢዮብ በሰይጣንና በእግዚአብሔር መካከል ስለነበረው ንግግር ‹‹ሰይጣንም ለእግዚአብሔር እንዲህ ብሎ መለሰለት። በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራ በከንቱ ነውን? እርሱንና ቤቱን በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን? የእጁን ሥራ ባርከህለታል፥ ከብቱም በምድር ላይ በዝቶአል። ነገር ግን እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ዳብስ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል።›› <u>*ኢዮ 1፡9-11፡፡*</u> ብሎ ያረጋገጠልንም ይህንን ነው፡፡
- ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ከተቀበለ በኋላ ኢዮብን ለመጉዳት ተሰለፈ፡፡
- ዳግመኛም ሰይጣን እግዚአብሔርን ‹‹ነገር ግን አሁን እጅህን ዘርግተህ አጥንቱንና ሥጋውን ዳብስ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል አለው። ›› <u>*ኢዮ 2፡5፡፡*</u> ብሎታል፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፫

## የእምነት ዓይነቶች

### 1. *የኀልዮ (ንድፈ-ሐሳባዊ) እምነት*

- ይህም የሚያስረዳን የኢዮብን ሥራ የባረከው እግዚአብሔር እንደሆነ ሀብቱን ሊያጠፋ ጤንነቱንም ሊያሳጣው እንደሚችል በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ሰይጣን ያመነ መሆኑን ነው።
- ኢዮብ እግዚአብሔርን በመቃወም የሚያቀርበው ማንኛውም ነገር እግዚአብሔርን እንደማማረርና እንደበደል ይቆጠርበት እንደነበር ሰይጣን ቢያምንም ኢዮብ ባለመበደል ያደረገውን(የሰራውንም) ሆነ እግዚአብሔር ያደረገውን ወይም የፈጸመለትን ሁሉ ግን አላመነም።
- ሰይጣን በዚህ መንገድ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ልጆቹንም ሲዋጋ ኖሯል ዛሬም ይዋጋል።
- ኢዮብ የነገረን ንድፈ ሐሳባዊው የሰይጣን እምነት ሐዋርያው እንደነገረን ‹‹ከሥራ ተለይቶ የሞተ›› እምነት *ያዕ 2፡20።* ነው።
- ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ከሆነ መልካም ነገሮችን በመቃወም በክፍፉ ሥራዎች የታጨቀ እምነትስ ምንድር ነው?
- የእግዚአብሔርን መኖር የተለያዩ ማስረጃዎችን በማቅረብ ውሱን ለሆነው የሰው መረዳት አሳማኝ አድርጎ ማቅረብ የሚቻልበት ይህ ንድፈ ሐሳባዊ እምነት ቀለል ያለ ሲሆን ዋናው ግን ተግባራዊ ወይም በሥራ የሚገለጥ እምነት ነው።

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፫

## የእምነት ዓይነቶች

### *ተግባራዊ እምነት*

- ይህ እምነት እግዚአብሔርን በፊታችን እንደሆነ አምነን እርሱን የምናይበት፣ የምንሰማበት የምንታዘዝበት እምነት ነው፡፡ ‹‹ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ በቀኜ ነውና አልታወክም፡፡›› ***መዝ 15፡8፡፡*** እንዳለ ልበ አምላክ ዳዊት፡፡
- ነቢዩ እንደተናገረው ዘላለማዊ በሆነው እግዚአብሔር ጥበቃ አምኖ ከዚህ ፍቅር ከሆነ አምላክ ጋር በጸሎት ይነጋገር ልመናውንም ያቀርብና እግዚአብሔርም የማይወዳቸውን ነገሮችም በተግባር ከመፈጸም ይቆጠብ ነበር፡፡ እኛስ ደስ የማያሰኘውን ከማድረግ ጉቦ ከመብላት፣ ከዝሙት፣ ከሌብነት፣ ከሐሜት፣ ከጠብ፣ ከክርክር…እንቆጠባለን?
- ልበ አምላክ ሳይፈራና ሳይታወክ በዘላለማዊ ሰላም ተጠብቆ መላ ሕይወቱን ለጥበበኛው ለእግዚአብሔር ሰጥቶ ይኖር ነበር፡፡
- በዚህ መንገድ የሚመራ የአማንያን ሕይወት ወደ ማይቆጠሩ ሀብታት ያደርሳል ብዙ ፍሬዎችን ለማፍራትም ያበቃል፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፫

## የእምነት ዓይነቶች

### 2. *የማይታወክ እምነት*

- ይህ ጊዜና ሁኔታን እየተመረኮዘ የሚገለጥ እምነት አይደለም፡፡
- እንዲህ ያለ እምነት በቤተ ክርስቲያን፣ በመንፈሳዊ ጉባኤያት፣ በጸሎት፣ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ፣ ቅዱስ ቁርባን ስንቀበል… ብቻ የሚታይ እምነት ሳይሆን በማንኛውም ጊዜና ቦታ ከቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ የሚገለጥ የሚታይ እምነት ነው፡፡
- እንዲህ ባለ መንገድ እግዚአብሔር ዘወትር በማይናወጽ እምነት በፊታችን ሆኖ ይታየናል፡፡ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም የቤተ ክርስቲያን አምላክ ብቻ ሳይሆን የልቦናና የአእምሮ እንዲሁም የሕይወት አምላክ ነውና፡፡

### 3. *ሳያዩ ማመን*

- እንዲህ ያለው እምነት ጌታችን ‹‹ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው፡፡›› ***ዮሐ 20:29*** እንዳለው በስሜቶች ወይም በሕዋሳቱ ላይ የማይደገፍ እምነት ነው፡፡
- እንዲህ ያለው እምነት በቤተ ሙከራቸው በምርምር መሣሪያዎቻቸው እስካላረጋገጡና በዓይናቸው እስካላዩ ድረስ እንደማያምኑት ሳይንቲስቶች ዓይነት እምነት አይደለም፡፡
- ይህ እምነት በሥጋ ዓይኖቻቸው ባለማየታቸው የተነሳ ፡፡ ‹‹ሰዱቃውያን፡ ትንሣኤም መልአክም መንፈስም የለም የሚሉ ናቸውና›› ***የሐዋ 23:8፡፡*** እንዳለው የሙታንን ትንሣኤ፣ የመላእክትንና የመንፈስን መኖር እንደካዱት እንደ ሰዱቃውያን ያለ እምነት አይደለም፡፡ እነሱ ባለማየት የተነሳ አላመኑም፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፫</u>

## <u>የእምነት ዓይነቶች</u>

### *4. <u>በመቅመስ መንፈሳዊ ድፍረት የሚገኝበት እምነት</u>*

- ይህም እምነት ከሥነ ሥላሴ (አምላክ) መጻሕፍት የምናነበው ወይም ከሃይማኖታዊ የትምህርት ተቋማት አሊያም በተለያየ መንገድ ከሰንበት ትምህርት ቤቶች የምንማረው እምነት አይደለም፡፡
- ይህ እምነት ልበ አምላክ ዳዊት ‹‹እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም፡፡›› *<u>መዝ 33(34)፡8</u>* በማለት እንደዘመረው እግዚአብሔር በሕይወታችን በእያንዳንድዋ ዝርዝር ጉዳይ እንዲገባ የምንፈቅድበት ከርሱም ጋር በኅብረት የምንሆንበትና እርሱን የምንቀምስበት ነው፡፡
- በዚህ እምነት እግዚአብሔር የሚተካከለው የሌለና አእምሮ ከሚያስበው በላይ ታላቅ እንደሆነ አረጋግጠናል፡፡
- ዘመናችን ሁሉ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት የምናደርግበት መሆን ይገባዋል፡፡ መልካምነቱን፣ ፍቅሩንና ጥበቃውን ከመቅመስ ጋር ኃያልነቱንና ክብሩን አይተናልና፡፡
- በችግሮቻችን ሁሉ መካከል ጣልቃ እየገባ አስቀድሞ ባልተፈቱበት መንገድ እንዴት መፍትሔ እንደሰጠን አይተናል፡፡ መጻሕፍትን በማንበባችን ወይም በመስማታችን ሳይሆን እግዚአብሔርን ከመቅመሳችን ብሎም በእጃችን በነካነው ወይም በዳሰስነው የተነሳ በእምነታችን ሙሉ ድፍረትን አግኝተናል፡፡ *<u>ቀዳ ዮሐ 5፡14፡፡</u>* ይህም እምነት በልባችን ለዘላለም የሚኖር እውነተኛ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ እምነት ነው፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፫

## የእምነት ዓይነቶች

### 5. ጠንካራ እምነት

- ይህ እምነት እንቅፋቶቹን ሁሉ የምናልፍበት፣ አይቻልም የሚባልን ነገር ሁሉ አልፈን ሁሉ የሚቻልበት ***ማር 9:23::*** ስለ ዘሩባቤልም ‹‹ታላቅ ተራራ ሆይ፥ አንተ ምንድር ነህ? በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ፡፡›› ***ዘካ 4:7::*** የተባለለት እምነት ነው፡፡
- ይህ እምነት በሙሴ ዘመን የኤርትራን ባሕር፣ በኢያሱም ዘመን ደግሞ የዮርዳኖስን ወንዝ ለማቋረጥ እግራቸውን ወደ ውሃ ያስገቡበት እምነት ነው፡፡ ***ዘጸ 14:22፣ ኢያ 3::***
- ውሃው በግራና በቀኝ እንደ አጥር ሆኖ ቢቆምም ሳይፈሩና ሳይጨነቁ በባሕርና በወንዝ መካከል የሚያሻግር እምነት ነው፡፡
- ይህ እምነት ዓለቱን በመምታት ውሃ የሚያፈልቅ ***ዘጸ 17:6***፣ ምግብ ሳይዙ ወደ በረሃ በመውጣት መና ከሰማይ እየተመገቡ፣ ሌሊት በእሳት ቀን በደመና ዐምድ እየተመሩ የሚጓዙበት እምነት ነው፡፡ ***ዘኁ 9:15-23::***
- ይህ እምነት ኤልያስ አክዓብን ‹‹ በፊቱ የቆምሁት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን! ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም ፡፡›› ***ቀዳ ነገ 17:1*** ያለበት ጠንካራ እምነት ነው፡፡
- ይህ እምነት ‹‹ ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች።›› ***ያዕ 5:17-18::*** እንደተባለውም ሰማይን የለጎመበትና የከፈተበት ነው፡፡

# የእምነት ሕይወት - ክፍል ፫

## የእምነት ዓይነቶች

### 6. *ጽኑዕ እምነት*

- ይህ እምነት ውጫዊ በሆኑ ተጽእኖዎች የማይናወጽ በቀርሜሎስ ተራራም ሆነ በጎልጎታ በእግዚአብሔር ፍቅር የምንታመንበት ነው፡፡
- ‹‹የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ።›› ***ዘፍጥ 22፡2፡፡*** ቢለውም ተስፋ የሌለው በሚመስለው በዚህ ሁኔታ ውስጥ የነበረው አብርሃም ከሣራ ዘርን በሚያበዛለት በእግዚአብሔር ፍቅር አመነ እንጂ አልተጠራጠረም፡፡
- ይስሐቅን ሊሰዋ ቢላዎ ሲያነሳም በሚያፈቅረው በእግዚአብሔር ፍቅርም ሆነ ሥራውን በሚሠራበት የእግዚአብሔር ጊዜ ግን አብርሃም ፈጽሞ አልተጠራጠረም፡፡
- እግዚአብሔር ከልጁ ይስሐቅ የሚሰጠውን ዘር እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ባሕር አሸዋ እንደሚያበዛለት ያመነበት እምነቱ በገጠመው ሁኔታ ፍጹም አልተናወጸም፡፡
- ጽኑዕ እምነት በእግዚአብሔር ላይ ባለን እምነት ድፍረት እንዲኖረን ስለሚረዳ በውጫዊ ሁናቴዎች የተነሣ አይለዋወጥም፡፡
- ጽኑዕ እምነት ያለበት ልቦና ሰላሙ በፍቅርና በእውነት በራሱ ጊዜ ከሚሠራ ከእግዚአብሔር ስለሆነ በውጫዊ ክስተቶች የተነሣ አይነዋወጽም፡፡ እኛ በምናየውና በምንሰማው የተነሣ ስንት ጊዜ ሸሽተናል ተሸሽገናል? እግዚአብሔር ያደረገውስ ምንድር ነበር?

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፫</u>

## <u>የእምነት ዓይነቶች</u>

### 7. <u>*ስጦታ የሆነ እምነት*</u>

- በመማር የሚገኝ እምነት አለ፤ ከመንፈስ ቅዱስ በስጦታ የሚሰጥ እምነትም አለ፡፡ ይህም ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ እምነት ተምሮ ወይም ሰምቶ ከማመን ከመጣው እምነት ይበልጣል፡፡
- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ስጦታ በተናገረበት ክፍል ‹‹የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል። ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል፥ <u>ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት</u>፥ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፥ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ…›› <u>***ቀዳ ቆሮ 12፡4-9፡፡***</u> እንዳለ የጸጋ የሚሰጥ እምነት አለ፡፡ ሳይማሩ፣ መጻሐፍትን ሳይመረምሩ ነገር ግን በእምነታቸው የሚነበቡ የሆኑ አባቶችና እናቶችን አላየንም! እነርሱ የተሰጣቸው ናቸው፡፡
- ይህ እምነት እንደ መንፈስ ፍሬ ሆኖ <u>*በገላ 5፡22*</u> ተጠቅሶም እናነባለን፡፡
- በዚህም እምነትን ከመንፈስ ፍሬም ሆነ ከመንፈስ ቅዱስ *ሥራዎች* ብሎም ከመንፈስ ስጦታዎች እንደማንለየው በዚህ ግልጥ ሆኖልናል:: እያንዳንዳቸው ግን የየራሳቸው መጠን አላቸው፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - ክፍል ፫</u>

## <u>የእምነት ዓይነቶች</u>

### *8. <u>የሚያስተጋባ -የሚናገር እምነት</u>*

- **ሰዎች በፖለቲካና በማኅበራዊ ጉዳዩች ላይ ያስቀመጡትን መርሕ አምነው፣ የያዙት አቋም ብርታትና ጥንካሬ ሲሰጣቸውና ወደ ሰዎችም ይህን አስተሳሰባቸውን ለማስተላለፍና ለማስረጽ እንዴት እንደሚጣጣሩ ተመልክተናል፡፡ እንግዲህ መንፈሳዊ የሆነው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኘን** ‹‹ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።›› ***<u>ይሁ 3</u>*** **በማለት የተገለጠው ሃይማኖት (እምነት) ፍጹም ንጹሕና ክቡር ነው፤ ይህ እምነት በእኛ ሆኖ ያስተጋባ!**
- **ይህም እምነት ማመን ብቻ ሳይሆን ሕይወት ሲሆን ሕይወቱም በማመን ላይ የተመሠረተና በመጽሐፍ ብቻ የሚገኝ ሐሳብ ሳይሆን ያመኑ ሰዎች በተጋድሎ የገለጡት፣ መከራም የተቀበሉበት ሕይወት ነው፡፡**
- **የምንማረውም ስለዚሁ ሕይወት በተግባር የሚናገር እምነት (የሃይማኖት) ሕይወት ነው፡፡** ‹‹እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ፥ ጽድቅን አደረጉ፥ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ፥ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፥ የእሳትን ኃይል አጠፉ፥ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፥ ከድካማቸው በረቱ፥ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፥ የባዕድ ጭፍሮችን አባረሩ። … ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወኅኒ ተፈተኑ፤ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፥ ተፈተኑ፥ በመጋዝ ተሰነጠቁ፥ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፥ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ።›› ***<u>ዕብ 11:33-40::</u>***
- **እንግዲህ ጌታችን** ‹‹በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ፤ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ።›› ***<u>ማቴ 10:27::</u>*** **እንዳለን ይህን ያመነውን በቃል ብቻ ሳይሆን በሕይወትም እንገልጠው ዘንድ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይርዳን፡፡**

ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org